# እንዳለፈው ጋንጩር

“ሁሉ በሽተኛ ፤ ሁሉ እራሴን ባይ
ከቤታችን ደህና ፤ መጥፋቱ ነው ወይ”
የሚለውን ተረት ፤ አየነው በይፋ
ቀድሞ ከምናውቀው ፤ የጠላት አንጋፋ
ያንገብባል ይሄው ፤ ከስልጣን አልጠፋ
መልኩን የቀየረ ፤ አዲስ ዘመነኛ
አራዳ መጣልን ፤ እንቅልፍ የሚያስተኛ
መጫወት የሚችል ፤ ቃላት አሳማሪ
ባፍ ጁዱ ዘራሪ ፤ አግኝተናል መሪ ።

እንኳንም ደስ አለሽ ፤ እሰየው አገሬ
ምንም የማይገባሽ ፤ አድርገውሽ ጥሬ
ቆዳሽን ሸልተው ፤ ሲያርዱሽ እንደበሬ
እጅግ የተካነ ፤ የሚያጣፍጥ ወሬ
ችግኝ ተከሉልሽ ፤ አያፈራ ፍሬ
ይቅርታን ሰባኪ ፤ መጣልሽ መምሬ ።

ሃያ ሰባት ዓመት ፤ ኢትዮጵያን የጋጠ
የጎጠኞ ች አምበል ፤ በትዕቢት ያበጠ
አንዱን ወደአንደኛው ፤ እያገላበጠ
እኩልነት መጣ ፤ አገር ተለወጠ
የሚል መሪ አገኘን ፤ አይኑን ያፈጠጠ ።

ቃላት በማጣፈጥ ፤ በወሬ እያዋዛ
የቦታ ልውውጥ ፤ በስልጣን ብወዛ
ባሰልቺ ዘረኛ ፤ ሻግቶ የጠነዛ
ስፍራውን ቀይሮ ፤ ዛሬም እየገዛ
ይቅርታ የሚለው ፤ መዝሙር ብቻ በዛ ።
የሰማነው ሁሉ ፤ ተናል እንደጤዛ
የውሃ ሽታ ነው ፤ ምንም የለው መዓዛ
ፍርሃት ያጀበው ፤ አይሆን ያገር ቤዛ ።

ካጋሰሶች መንጋ ፤ በርግጥ ከተለዩ
የተናገሩትን ፤ በተግባር ያሳዩ
መልሰው አይሹሙ ፤ ዛሬም ከገዳዩ
ለአዲሱ ተሿሚ ፤ ይድረስ ለአቶ አብይ
ይደመጥ ህዝባችን ፤ ባይሆን እንኳን ነብይ
እንደዚያ አረመኔ ፤ ለጥፋት የፃፈው
እንዳለፈው ጋንጩር ፤ ሞት እንደቀሰፈው
እፈራልሁ ለርስዎም ፤ እንዳይተፋዎት ሰው ።

ታዛቢው

May 25, 2018